# የዕፅዋት ዘር ብዜትና ንግድ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ

መመሪያ ቁጥር **463/2013**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Agriculture & Natural Resources

መግቢያ

በኢትዮጵያ ሶስት ዋና ዋና የዘር ስርአቶች አሉ፡፡ እነዚህም መደበኛ ተሸጋጋሪ እና ኢመደበኛ የተባሉ የዘር ስርአቶች ናቸው፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት በየአመቱ በመደበኛ የዘር ስርአት በኩል የሚቀርበው የዘር መጠን እጅጉን አነስተኛ ነው፡፡ የመደበኛውን ዘር ስርአት መስመር ለማስያዝ በዘር ንግድ ስራ ላይ የሚሰማሩት ተዋንያን አቅም ያላቸው እንዲሆኑ እና ህጋዊ ከለላ እንዲያገኙ በማድረግ የአርሶአደር/ከፊል አርብቶ አደር ጥራቱን የጠበቀ ዘር ተጠቃሚነት ቀጣይነት ባለው መልኩ ማስኬድ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በዘር ስራ የተሰማራውን አካል የሚያነቃቃና ከህገወጦች የሚከላከል የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንንም ስርአት በመመሪያ እንዲደገፍ በማድረግ በክልሎች መካከል የአሰራር ወጥነት ለማረጋገጥ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## አውጭው ባለስልጣን

የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ስለዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 27(2) እና ስለዕፅዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 375/2008 በአንቀጽ 42(4)፣ 43(3) እና 44(3) የተደነገገውን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ የዕፅዋት ዘር ብዜት እና ንግድ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር**463/2013**ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 እና ስለዕፅዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 375/2008 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረግ በድጋሚ ትርጉም መስጠት ሳያስፈልግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ሆኖ:-

2.1."መደበኛ የዘር ስርአት" ማለት በሀገሪቱ በወጣው የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት የተመዘገበ የተሻሻለ የዕፅዋት ዝርያ ዘር በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ዘር ከማሣ ዝግጅት እስከ ግብይት ድረስ ቁጥጥር የሚደረግበት የአሰራር ሂደት ነው፤

2.2."የተሸጋጋሪ (intermediate) የዘር ስርአት" ማለት በመደበኛውና በኢ-መደበኛው የዘር ስርአት መካከል የሚገኝ ስርአት ነው፤

2.3."ኢ-መደበኛ የዘር ስርአት" ማለት የተመዘገበ ወይም የአካባቢ ዝርያ /ነባር ዝርያ/ በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አማካኝነት በዘር ደረጃ በወጣው መስፈርት መሰረት ቁጥጥር ሳይደረግበት አርሶ አደሩ/ከፊል አርሶአደር እርስ በርስ የሚያደርገው የዘር ልውውጥ ስርአት ነው፤

2.4.ጥራቱ የተገለጸ የዘር ሥርዓት ማለት በሚኒስቴሩ መመሪያ ቁጥር 1/2007 የተገለጸውን ሥርዓት ያመለክታል፡፡

2.5."መደበኛ የዕፅዋት ዘር አምራች" ማለት በመደበኛው የዘር ስርአት የተመዘገበን ዘር ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት አግባብነት ባለው ባለስልጣን የተሰጠው ግለሰብ፣ ሕብረት ሥራ ማህበራት፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ ወይም መንግስታዊ ተቋምን ይመለከታል፤

2.6."የዘር ሎት" ማለት ወጥነት ያለው በአካል ሊለይ የሚችልና መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ነው፡፡

2.7."የዕፅዋት ዘር ስራ" ማለት በመደበኛው የዕፅዋት ዘር ስርአት ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ወደ ውጭ አገር መላክ፣ ማስመጣት፣ ማከፋፈል ወይም መቸርቸርን ይመለከታል፤

2.8."ዘር አከፋፋይ" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ኖሮት፣ የኢትዮጵያ ዘር ደረጃ መስፈርቶችን ያሟሉ፣ ምንጫቸው የታወቁና የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያ ዘሮችን በመጋዘን በማከማቸት ለቸርቻሪዎች ወይም በስፋት ለሚያመርቱ ተጠቃሚዎች በጅምላ የሚሸጥ ሰው ነው፤

2.9."ዘር ቸርቻሪ" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለውና ከዘር አከፋፋዮች ወይም ከአምራቾች የሚረከበውን የዕፅዋት ዘር ጥራቱ እንደተጠበቀ

ለተጠቃሚ በችርቻሮ እስከ ዝቅተኛው መጠን መያዣው ሳይከፈት የሚሸጥ ሰው ነው፤

2.10. "የውስጥ የዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር" ማለት ዘር አምራቹ ያባዘውን ዘር በመስክና በላቦራቶሪ ደረጃ በራሱ ባለሙያዎች አማካኝነት በአገሪቱ ዘር ጥራት መስፈርት መሠረት የሚደረግ ቁጥጥር ነው፤

2.11. "የውጭ የዕፅዋት ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል" ማለት የተመዘገበ የዕፅዋት ዝርያ ዘር የሚያመርቱ አምራቾች በወጣው የመስክና የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት ጠብቀው ማባዛታቸውን የሚቆጣጠርና ማረጋገጫ የሚሰጥ ህጋዊ አካል ነው፤

2.12. "ኩታ ገጠም ማሳ" ማለት የጋራ ድንበር ያላቸውን ማሳዎች ማለት ነው፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

3.1. በመደበኛው የዕፅዋት ዘር ስርአት የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበና የዘር ጥራት ደረጃ የወጣለት የዕፅዋት ዝርያ ዘር ላይ፤

3.2. ዘር በማምረት፣ በማዘጋጀት፣ በማከፋፈል፣ በመቸርቸር፣ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር በመላክ በተሰማራ አካል ላይ፤

3.3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3.1 እና 3.2 የተገለጸው ጠቅላላ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው፡-

ሀ. ጥራቱ በተገለጸ ዘር ስርአት የተመረተ ዘር ላይ፣

ለ. በአርሶ አደሩ መካከል የሚደረግ የዘር ልውውጥ ላይ፣

ሐ. የደን ዘር ላይ፣

መ. ለምርምር ስራ የሚውል ዘር ላይ ነው፡፡

4. የመመሪያው ዓላማ

የብቃት ማረጋገጫ መስፈርትን ያሟላ ግለሰብ ወይም ድርጅት በህጋዊ መንገድ በዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ መላክ፣ ማስገባት፣ ማከፋፈል ወይም መቸርቸር ስራ ላይ ለመሰማራት ፈቃድ ለሚጠይቅ የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ዘር ለተጠቃሚው የሚደርስበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ዘር አምራቾችን፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture & Natural Resources

አዘጋጆችን፣ አስመጪዎችን፣ አከፋፋዮችንና ቸርቻሪዎችን የተጠቃሚዎችን መብት በማስከበር፤ የህግ ከለላ የሚያገኙበትን ስርአት ማስፈን ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ዘር ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርቶች

5. መስክ ሰብሎች ዘር

5.1. የሚመረትበት ማሳ

5.1.1. ዘር የሚመረትበት ማሳ የኮንትራት ወይም የባለቤትነት ማስረጃዎች አባሪ ሆኖ የሚቀርብበት በሊዝ ወይም በባለይዞታ በውልና ማስረጃ የተመዘገበ ወይም በኪራይ የተገኘ የመንግስት ወይም የግል እርሻ ሊሆን ይችላል፤

5.1.2. የዘር ብዜት ማሳው በፌደራልና በክልል ደረጃ እውቅና ከተሰጣቸው አደገኛ አረሞችና በሽታዎች የጸዳ ሊሆን ይገባል፤

5.1.3. የዘር ብዜት ማሳው የሚገኝበት ስነምህዳር ሊመረት ለታቀደው ሰብል ተስማሚ የሆነና የማሳው ተዳፋትነት እንደየክልሉ እና እንደ ሰብሉ ተጨባጭ ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ ከአጎራባች ማሳዎች የዘር ጥራት የሚያጓድሉ የጎርፍ መነሻ ምክንያቶች የሌሉ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፤

5.1.4. ለዘር ብዜት የተመረጠው ማሳ ለጥራት ቁጥጥር፣ ለድጋፍና ክትትል አመቺ መሆን አለበት፤

5.1.5. በአመልካቹ የቀረበው ለዘር ብዜት የሚሆን ማሳ እንደ ሰብል አይነቱ ዝቅተኛውን የማሳ ስፋት መስፈርትን ማሟላት የሚኖርበት ሲሆን እንደ ክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ አነስተኛ የኩታገጠም መጠንና ጠቅላላ ይዞታ መጠን ቀጥሎ ከተጠቀሰው ከፍ ሊል ይችላል፡፡

5.1.5.1. ለመስክ ሰብሎች፡-

ሀ. አምራቹ በራሱ ማሳ ላይ ድቃይ ያልሆኑ ሰብሎችን /self pollinated crops/ የሚያመርት ከሆነ በህጋዊ ሰነድ የተደገፈ ሊኖረው የሚገባው ጠቅላላ ይዞታ መጠን ከ10 ሄክታር የማያንስ መሆን ይኖርበታል፤

ለ. አምራቹ በራሱ ወይም በአርሶ አደር ማሳ ላይ ድቃይ የሆኑ /hybrid varety / የበቆሎና የማሽላ ዘር የሚያመርት ከሆነ በህጋዊ ሰነድ

የተደገፈ ሊኖረው የሚገባው ጠቅላላ ይዞታ ከ40 ሄክታር ማነስ የለበትም፡፡

5.1.5.2. ለአትክልት እና መኖ ዘሮች፡-

ሀ. አምራቹ በራሱ ወይም በአርሶ አደር ማሳ ላይ የኮረት ዘር (bulb and tuber) የሚያመርት ከሆነ በህጋዊ ሰነድ የተደገፈና ሊኖረው የሚገባው ጠቅላላ ማሳ መጠን ቢያንስ ለአትክልት ዘር 5 ሄክታር እና ለመኖ ዘር 2 ሄክታር መሆን አለበት፤

ለ. አምራቹ በራሱ ወይም በአርሶ አደር ማሳ ለአትክልት ዘር (botanical seed) የሚያመርት ከሆነ በህጋዊ ሰነድ የተደገፈና ሊኖረው የሚገባ ጠቅላላ ማሳ መጠን ቢያንስ ለአትክልት ዘር 2 ሄክታር እና ለመኖ ዘር ቢያንስ 0.5 ሄክታር መሆን ይኖርበታል፤

መ. አምራቹ በራሱ ወይም በአርሶ አደር ማሳ ቁርጥራጭ ዘር የሚያመርት ከሆነ በህጋዊ ሰነድ የተደገፈና ሊኖረው የሚገባ ጠቅላላ ማሳ መጠን ለአትክልት ዘር ቢያንስ 5 ሄክታር እና ለመኖ ዘር ቢንያንስ 2 ሄክታር መሆን አለበት::

5.1.5.3. ለፍራፍሬ ሰብሎች፡-

አምራቹ በራሱ ወይም በህጋዊ ሰነድ በተደገፈ የሌሎች አካላት ይዞታ የፍራፍሬ ዘር የሚያዘጋጅ ከሆነ

ሀ. ለእምቡጥ (bud) ወይም ለሳየን (scion) ምንጭነት የሚውል እናት ዛፍ ቢያንስ 5 ተክል በየሰብሉ፣

ለ. ለተከተበ ችግኝ እና ለመሰረተ ግንድ (root stock) ቢያንስ አንድ ሄክታር፣

ሐ. ለቁርጥራጭ (cutting for grape) ቢያንስ 100 ተክል በየዝርያው፣

መ. ለኮርም (corms) ለሙዝ ከሆነ ቢያንስ 500 ተክል በየዝርያው፣ ለእንሰት ከሆነ ቢያንስ 100 ተክል በየዝርያው ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

5.2. ባለሙያ

5.2.1. በዘር ስራ በዕፅዋት ሳይንስ/ በሆርቲካልቸር/ በጠቅላላ እርሻ ሙያ ቢያንስ ዲፕሎማና ከዚያ በላይ ያለው ወይም በዚህ ደረጃ ያለን ባለሙያ መቅጠር የሚችል፤

5.2.2. በንዑስ አንቀጽ 6.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዘር ስራ ቢያንስ የአንድ ዓመት የስራ ልምድ ያለው ወይም በዚህ ደረጃ ያለን ባለሙያ መቅጠር የሚችል፡፡

5.3. የእርሻ መሳሪያ

ለሚለማው መሬት መጠን ወይም ለሚመረተው ሰብል ዓይነት እንደአስፈላጊነቱ የእርሻ ማምረቻ መሣሪያዎች ማቅረብ የሚችል፤ ከነዚህም መካከል

ሀ/ ትራክተር ወይም የእንስሳት ጉልበት

ለ/ የውሃ መሣቢያ (በመስኖ ለሚለማ ማሳ)፤

ሐ/ ማረሻ፣ መከስከሻ፣ መቧጠጫ፤መኮትኮቻ፤

መ/ መዝሪያ፤

ሠ/ መውቂያ፤ምርት ማመላለሻ

ረ/ መድሀኒት መርጫ፤

ሰ/ የችግኝ ጣቢያ ቁሳቁስ

ሽ/ ጂ.ፒ.ኤስ

ረ/ እንደየሰብሉ ዓይነት ሥራውን ሊያሰራ የሚችል ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ያለው ወይም በኪራይ ማቅረብ የሚችል

5.4. የውስጥ ዘር ጥራት ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት

5.4.1. ለመስክ የዘር ጥራት ቁጥጥር:-

5.4.1.1. አመልካቹ ዘር የማምረት ስራውን የሚያከናውነው ድቃይ በቆሎ ከሆነ የውስጥ የመስክ ዘር ጥራት ቁጥጥር የሚከታተሉ እስከ 200 ሄ/ር ለአንድ ባለሙያ ስሌት ባለሙያዎችን መቅጠር ይኖርበታል፤

5.4.1.2. አመልካቹ ዘር የማምረት ስራውን የሚያከናውነው ድቃይ ያልሆኑ ሰብሎች ከሆነ የውስጥ የመስክ ዘር ጥራት ቁጥጥር የሚከታተሉ እስከ

500 ሄክታር ለአንድ ባለሙያ ስሌት ባለሙያዎችን መቅጠር ይኖርበታል፤

5.4.1.3. ለመስክ ጥራት ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

5.4.2. የውስጥ ዘር ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ

በውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር የሚሠራ የላብራቶሪ የጥራት ፍተሻ ማእቀፎች ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል:-

ሀ. የዘር እርጥበት መጠን ፍተሻ፣

ለ. የዘር ንጽህና ፍተሻ፣

ሐ. የዘር ብቅለት ፍተሻ፣

5.4.3. ለዘር ጥራት ፍተሻ የሚያገለግሉ የላቦራቶሪ ቁሳቁሶች

በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8.2 የተጠቀሱትን የዘር ጥራት ፍተሻ ስራ ለመስራት አመልካቹ የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ማሟላት ይኖርበታል፤ ወይም ከሌላ ላቦራቶሪ አገልግሎቱን ስለማግኘቱ የውል ሰነድ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ላቦራ ቶሪው ቢያንስ የሚከተሉትን ቁሳቁስ ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ. የዘር ናሙና ማስቀመጫ መደርደሪያ

ለ. ነጭ ጠረጴዛና (1.5 ሜትር በ90 ሳንቲ ሜትር ስፋት እና ቁመት 90 ሳንቲሜትር) ተሽከርካሪ ወንበር፣

ሐ.በተስማሚነት ምዝና ተቋም የተፈተሸ አናላቲካል ባላንስ እና ወይም ሴንሲቲቭ ባላንስ፣

መ.ፈጣን የእርጥበት መጠን መለኪያ፣

ሠ.የዘር ማብቀያ ሳህን፣

ረ.ግራጅዌት ሲሊንደር፣

ሰ.ፎርሴፕስ፣

ሸ.አሸዋ እና ወይም ለብቅለት የሚያገለግል ወረቀት፣

ቀ.ፒዩሪቲ ቦርድ፣

በ. የናሙና መቀሸቢያ/sample trier/፣

ተ.ወንፊት፣

ቸ. የግንበኛ ማንኪያ፣

ነ. ናሙና የሚያዝበት ውሀ የማያሳልፍ የወረቀት ከረጢት፣

ኘ. የሙቀት መለኪያ/thermometer/፣

5.4.4. የዘር ላቦራቶሪ ዲዛይን

5.4.4.1. አንድ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ስፋቱ ቢያንስ 4 ሜትር በ6 ሜትር ሆኖ ውስጡ ለሁለት ክፍል የተከፈለ ሊሆን ይገባል፤

5.4.4.2. ለሁለት ከተከፈሉት ክፍሎች አንዱ ለዘር ንጽህናና ለርጥበት መጠን መለኪያ ሌላው ክፍል ደግሞ ለብቅለት ፍተሻ ስራ እንዲውል ይደረጋል፤

5.4.4.3. የክፍሎች ወለል በኮንክሪት የተሰራ መሆን አለበት፤

5.4.4.4. የክፍሎች ግድግዳ በነጭ ቀለም የተቀባ መሆን አለበት፡፡

5.4.4.5. ጣሪያው በኮርኒስ የተለየ ሆኖ ከወለሉ እስከ ኮርኒሱ ያለው ከፍታ 3.5 ሜትር ቁመት ያላነሰ መሆን አለበት፤

5.4.4.6. መስኮቶቹ በቂ የፀሀይ ብርሀን እንዲያስገቡ ከመስተዋት መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡

5.4.4.7. መስኮቶቹ ከወለሉ አንድ ሜትር ከፍ ብለው የሚሰሩና ስፋታቸው 1.5 ሜትር በ1.5 ሜትር ያላነሰ ሆኖ ሁለት በምስራቅ ሁለት በምዕራብ በኩል ይሰራል፤

5.4.4.8. የመብራቱ አምፖል ፍሎረሰንስ መሆን ይኖርበታል፡፡

5.4.4.9. የቤቱ አቀማመጥ ከሰሜን ወደ ደቡብ ሆኖ ይገነባል፡፡

5.4.5. የላቦራቶሪ ፍተሻ ባለሙያ

5.4.5.1. አመልካቹ የዘር ጥራት ፍተሻ የሚያከናውነው ብዛት ከ100 ላልበለጠ ናሙና ከሆነ በአንቀፅ 6 ላይ የተጠቀሰው የመስክ ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ የዘር ጥራት ፍተሻ እንዲያከናውነው ይደረጋል፤

5.4.5.2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 8.5.1 ከተጠቀሰው በላይ የሆነ ናሙና የሚፈትሽ ከሆነና አንድ የመስክ ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ብቻ ካለው ተጨማሪ ባለሙያ በኮንትራት ወይም በቋሚነት ይቀጥራል፡፡

6. በቲሹ ካልቸር ስለሚዘጋጁ ዘሮች ፤

በቲሹ ካልቸር የዘር ብዜት ሥራ ላይ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ቢያንስ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ያስፈልጋል፡-

ሀ) በሆርቲካልቸር የመጀመርያ ዲግሪና ከዛ በላይ ያለው

ለ) ዝቅተኛ ዓለም አቀፍ ደረጃ ያሟላ ላቦራቶሪ ያለው

ሐ) ለቲሹ ካልቸር የሚያስፈልጉ የላቦራቶሪ ቁሳቁሶች/Equipments/ ማሟላት የሚችል

1) ዲጅታል ቶፕ ፓን/ አናላይቲክ መመዘኛ/Digital top pan/analytical balance
2) ፒኤች ሜትር/ pH meter
3) የውሃ ዲስትለር/water distler
4) ጋዝ በርነር /Gas burners
5) አውቶክሌቭ/ Autoclave
6) ላሚናር ፍሎ ሁድስ /Laminar flow hoods
7) ኢንኩቤሽን ቻምበር /Incubation chambers
8) ፍሪዘር(-20 °C) / Freezer (-20° C)
9) ሪፍረጀሬተር (4 °C /Refrigerator 4° C
10) ቮርቴክስ ሚክሰር/ Vortex mixer
11) ማይክሮፒፔትስ(micropipettes)
12) ዲ.ኤን.ኤ ኤክስትራክሽን/DNA extraction equipment
13) ዲ.ኤን.ኤ ፕሮብስ/DNA probes
14) ቲሹ ግራይንደር/Tissue grinder
15) ሴንትሪፉጅ/ማይክሮ ሴንትሪፉጅ /Centrifuge / Micro centrifuge
16) ፒ.ሲ.አር/PCR
17) ሪዞንታል ጄል ኤልክትሮፎረሲስ/Horizontal Gel Electrophoresis
18) ጄል ዶክመንቴሽን ዩኒት/Gel documentation unit
19) ዲ.ኤን.ኤ ፊንገር ፕሪንቲግ ቁሳቁሶች/Equipments for DNA fingerprinting

20) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚከተሉት ኬሚካሎች/Reagents

   i. ዲያግኖስቲክ ኬሚካል/Dignostic reagents
   ii. ሲዲኤንኤ ፕሮብስ/cDNA probes
   iii. ፖሊክሎናል/ሞኖክሎናል አንቲ ቦዲስ/Polyclonal / monoclonal anti-bodies for diagnostic for commonly occurring Viruses
   iv. ፕራይመርስ/ Primers

7. በአትክልት ችግኝ ዝግጅት ለሚሰማሩ

ከላይ በአንቀጽ 5.2 ስለ ባለሙያ መስፈርት የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአትክልት ችግኝ ዝግጅት ላይ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ቢያንስ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ያስፈልጋል፡

ሀ/ በብረት ቋሚ የተሰራ የፕላስቲክ ግሪን ሀውስ

ለ/ የሙቀት ወይም የጨረር መከላከያ ጥላ/Thermal screen/shed screen/

ሐ/ የመዝርያ ላይን ወይም ዘር መዝርያ ሳህንና ማስቀመጫ አልጋ

መ/ የዘር ማከማቻ ክፍል

ሠ/ የማብቀያ ክፍል/generation or propagation room

ረ/ የችግኝ ማሸጊያ ላይን/ክፍል

ሰ/ የችግኝ ዝግጅት ቁሳቁችና ማከማቻ መጋዝን

ሸ/ የማዳበሪያ መስጫ ማሽን/Fertigation Dossing pump

ቀ/ የኬሚካል መስጫ ማሽን/ chemical spraying machine

በ/ የእጅና እግር መጽጃ ግብዓት/hand & foot disinfection & cleaning facility

ተ/ችግኝ ማጠንከሪያ ክፍል/hardening room

ቸ/ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ኬሚካሎች

## ክፍል ሶስት

## ዘር ለማዘጋጀት የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርቶች

8. ባለሙያ

8.1. በዕጽዕዋት ሳይንስ ወይም በሆርቲካልቸር ወይም በጠቅላላ እርሻ ዲፕሎማና ከዚያ በላይ ያለው፤

8.2. አንድ አመት በዘር ዝግጅት የስራ ልምድ ያለው ሆኖ በቋሚነት ወይም በኮንትራት ሰራተኛነት የቀጠረ ወይም በአንቀጽ 6 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶችን በማሟላት የተቀጠረውን የዘር ባለሙያ አሰልጥኖ መጠቀም የሚችል፡፡

9. መጋዘን

ዘር ከተዘጋጀ በኋላ በዘር ሎቲንግ ስርአት ለማከማቸት የሚያስችልና የሚከተሉት መስፈርቶችን ያሟላ መጋዘን ያስፈልጋል፡፡ይሄውም፡-

9.1. ህንፃ፡-

ሀ. ህንፃው ከድንጋይ ወይም ከሸክላ ወይም ከብሎኬት ወይም የጭቃ ግድግዳ (በውስጥና በውጭ በሲሚንቶ የተለሰነ) የተሰራ አራት ማእዘን ቅርጽ መሆን ይኖርበታል፤

ለ. የህንፃው አቀማመጥ ከምእራብ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ የተገነባ ሊሆን ይገባል፡፡

9.2. ጣሪያ፡-

ሀ. ደጋፊ ምሶሶዎች ለድርድር እና ለጽዳት እንዳያስቸግር እንዲሁም ተባይ መግቢያና መደበቂያ በማይሆኑበት ሁኔታ መሠራት ይኖርባቸዋል፤

ለ. ጣሪያው ውሀ ፍጹም የማያስገባ መሆን አለበት፤

ሐ. ለዘር ሎት ድርዳሮ ተገቢው ቦታና ከፍታ እንዲኖር ለማስቻል የጣሪያው ጫፍ ከመሬት በላይ ቢያንስ 5 ሜትር ከፍታ ሊኖረው ይገባል፤

9.3. ግድግዳ፡-

ሀ. የግድግዳ ስንጥቅጥቆች የቆሻሻ ማጠራቀሚያና የተባይ እንቁላል መጣያ እንዳይሆን መደፈንና መለሰን አለበት፤

ለ. ጣሪያና ግድግዳው ከ6 ሚሊ ሜትር ባልበለጠ ክፍተት መገንባት ይኖርበታል፤ ወፎች ጎጆ ሊሰሩ የሚችሉበት ምንም አይነት ጠርዝ መኖር የለበትም፤

ሐ. የውስጥ ብርሃን እንዲኖረው የውስጥ ግድግዳ ነጣ ያለ ቀለም መቀባት አለበት፤

መ. የግድግዳው ቀለም ሲታጠብ በቀላሉ የማይለቅ መሆን አለበት፡፡

9.4. በር፡-

ሀ. የዘር መጋዘን በሮች በአንዱ የግድግዳ ፊት ለፊት ገጽ ሆነው እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ እስከ ሁለት ትላልቅ በሮች ይኖሩታል፤

ለ. ሁሉም ትላልቅ በሮች ተንሸራተው የሚዘጉና አይጥ እንዳይሾልክ የመንሸራተቻው አቃፊ በብረት የታሸገ እና በሁሉም አቅጣጫ (ከጎን ከታችና ከላይ) የግጣሙ ክፍተት ከ6 ሚሊ ሜትር የማይበልጥ መሆን ይኖርበታል፤

ሐ. በሩ ዝገትን ለመከላከል በበቂ የመጀመሪያ (primer) እና መጨረሻ (emamel) ሽፋን ቅብ መቀባት ይኖርበታል፤

መ. የበሩ አቃፊ ከድንገተኛ የግጭት አደጋ ለመከላከል ከ10-15 ሴንቲ ሜትር ዲያሜትር ባለው የብረት ቧንቧ የተሰራ መከላከያ ሊኖረው ይገባል፡፡

9.5. ወለል፡-

ሀ. ወለሉ ከውጭ ከፍታ በላይ 1.4 ሜትር ወይም በጭነት መኪና ጀርባ ከፍታ (truck bed height) ልክ መሆን ይኖርበታል፤

ለ. ወለሉ እርጥበት በማያሳልፍ እና በክብደት የተነሳ በቀላሉ ከማይሰባበር ኮንክሪት የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል፤

ሐ. እርጥበትን ለመከላከል ከወለሉ በላይ ከጣውላ የተሰራ ፓሌት /ርብራብ/ ሊኖረው ይገባል፡፡

9.6. ብርሀን፡-

የመጋዘን ብርሃን በዘር መያዣ ከረጢት ላይ ያለውን መለያ ምልክቶች ወይም መረጃዎችን ማየት በሚያስችል ሁኔታ፡-

ሀ. የመጋዘን ጣሪያው አልፎ አልፎ ብርሃን አስተላላፊ ነጭ ቆርቆሮ የተሰራ መሆን ይኖርበታል፤

ለ. መብራቶች ከፍሎረሰንት የተሰሩ መሆንና ከግድግዳ በላይ በኮርኒስ ከፍታ ልክ መገጠም ይኖርበታል፤

ሐ. ማብሪያና ማጥፊያው ከመግቢያ በሩ አካባቢ መሆን ይኖርበታል፡፡

9.7. የአየር ዝውውር (air movement)

እንደ ስነምህዳሩ ሁኔታ የሀንፃውን የላይኛው ሞቃት አየርና የወለሉን እርጥብ አየር ከመጋዘን ውስጥ ለማስወገድ፡-

ሀ. የአየር መቅዘፊያ (exhaust fan) እንደየ መጋዘኑ ስፋት በአማካይ ቦታ የተገጠመለት፤

ለ. ከ6 ሚ.ሊ ሜትር ወንፊት የተሰራ የአየር ማናፈሻ ቀዳዳ በጥንድ መልኩ ከመጋዘኑ ፊትና ኋላ በትይዩ በየ2 ሜትር ርቀት ሊኖረው ይገባል፤

ሐ. በግድግዳው የላይኛው ጫፍ ያለ የአየር ማናፈሻ ቀዳዳ (ventilation opening ዝናብ በማያስገባ መልኩ ክፍት መሆን አለበት፤

መ. የአየር ማናፈሻ ቀዳዳ መስኮቶች ወንፊት ያሉትና 50 ሴንቲ ሜትር በ1 ሜትር እና በላይ ስፋት ያለው ጣራ ስር የፀሀይ ብርሀን ዘልቆ እንዳይገባ መቆጣጠር የሚያስችል፡፡

9.8. የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ

በዘር ማከማቻ መጋዘን ውስጥና አካባቢ ሊከሰት የሚችልን እሳት አደጋ ለመቆጣጠር መጋዘኑ የእሳት ማጥፊያ /fire exstinguisher/ በየበሩ የተገጠመለት በየጊዜው የሚታደስ ሊሆን ይገባል፤

9.9. ምዝን የአየር እርጥበት እና የሙቀት መጠን መለኪያ የተገጠመለት፤

9.10. መጫኛ/ማራገፊያ

የመጋዘኑ መጫኛና ማራገፊያ የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ. በመጠለያ የተሸፈነ መጫኛ/ማራገፊያ ሥፍራ በበሩ መኖር አለበት፣



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture & Natural Resources

ለ. በእጅ ለሚገፉ ጋሪዎች ለፎርክ ሊፍት ሊያገለግል የሚችል ተዳፋትነት ያለው መንገድ (sloping ramp) በአንድ በር ላይ ብቻ እንዲኖር ያስፈልጋል፤

ሐ. የጭነት መኪናዎች የዘር መጋዘንና የዘር ክምችትን ሊያበላሹ ስለሚችሉ ወደ መጋዘን መግባት የለባቸውም፡፡

10. የዘር ማዘጋጃ መሳሪያዎች

10.1. የማበጠሪያ ቤት፡-

ሀ. የዘር ማበጠሪያ መሳሪያ ከሚቀመጥበት ቦታ ውጭ ያለው የቤቱ ክፍተት ቢያንስ 100 ካሬ ሜትር መሆን ይኖርበታል፤

ለ. እርጥበት የማያስገባ መሆን አለበት፤

ሐ. ወለሉ ክብደት መሸከም የሚችል በኮንክሪት የተሰራ መሆን አለበት፤

መ. ለሰራተኞች አገልግሎት የሚሰጥ ሻወርና ሽንት ቤት ሊኖረው ይገባል፣

ሠ. ለሰራተኞች እንደ ጓንት፣ ጎግል፣ ቱታ፣ ቦት ጫማ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማስክ እና የመሳሰሉት የደህንነት ትጥቆች ሊኖሩት ይገባል፣

ረ. የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ የተገጠመለት መሆን አለበት፡፡

10.2. የዘር ማዘጋጃ መሳሪያ

የዘር ማዘጋጃው መሳሪያ ቢያንስ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

ሀ. የዘር መቀበያ ቋት፣

ለ. የአየር ወንፊት ማጣሪያ/air screen cleaner/፣

ሐ. ጥሬ ግርድፍ ማጣሪያ/pre-cleaner/፣

መ. ጥሬ ስልቅ ማጣሪያ/fine cleaner/፣

ሠ. የመጠን መለያ/grader፣

ረ. የቁመት መለያ/indented cylinder/፣

ሰ. ማንጓለያ ጠረጴዛ/gravity separator/፣

ሸ. የተለያዩ ወንፊቶች/different size sieve/

ቀ. ፀረ ተባይ መለወሻ/seed dressor/

በ. ሚዛን/weighing unit/ እንደአስፈላጊነቱ፣

ተ. ማሸጊያ/bagging unit/፣

ቸ. የአቧራና የብናኝ ቆሻሻ ማስወገጃ ሳይክሎን፡፡

## ክፍል አራት

## በግል ዘርን በማሳ ኢንስፔክት ለማድርግና ናሙና ለመውሰድ ፍቃድ መስጠት

12. በግል ወይም ተደራጅቶ የዘር ማሳን ኢንስፔክት ለማድረግ

12.1. በዕፅዋት ሳይንስ ነክ ሙያ ቢያንስ ዲግሪና ከዚያ በላይ ያለው፤

12.2. በንዑስ አንቀጽ 12.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ የአምስት አመት የስራ ልምድ በማሳ የዘር ጥራት ቁጥጥር ልምድ ያለው፤

12.3. በማሳ የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥራን ለመስራት አመልካቹ የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

- ሀ. ጂ.ፒ.ኤስ
- ለ. አንድ ሜትር በአንድ ሜትር ኳድራንት፣
- ሐ ካውንተር፣
- መ. የበሽታ ናሙና መሰብሰብያ ከረጢት፣
- ሠ. ፈጣን የእርጥበት መጠን መለኪያ፡፡
- ረ. ማጉያ ሌንስ
- ሰ. ኮምፓዲየም
- ሸ. በራሱ መጓጓዣ ተጠቅሞ የሚሰጠውን ኃላፊነት መወጣት የሚችል፤

13. በግል ወይም ተደራጅቶ የዘር ናሙና ለመውሰድ

13.1. በዕፅዋት ሳይንስ ነክ ሙያ ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው፤

13.2. በንዑስ አንቀጽ 13.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ የሶስት አመት ናሙና የማምጣት ልምድ ያለው

13.3. ናሙና የማምጣት ስራ ላይ ለመስራት አመልካቹ የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

- ሀ. የናሙና መቀሸቢያ/sample trier/፣
- ለ. የናሙና ማስቀመጫ መደርደሪያ ፣
- ሐ. ሴንሲቲቭ ባላንስ እና እስከ አንድ ኪሎ መመዘን የሚያስችል ሚዛን

መ. ናሙና የሚያዝበት ውሀ የማያሳልፍ የወረቀት፣ፕላስቲክ እንዲሁም የጨርቅ ከረጢት ያለው፡፡

14. የመስክ ጥራት ለመቆጣጠርና የዘር ናሙና ለመሰብሰብ የብቃት ማረጋገጫ ስለማግኘት

14.1. የመስክ ጥራት ለመቆጣጠር የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል በአንቀጽ 13 የተጠቀሱትን አሟልቶ ከተገኘና የዘር ናሙና ለመሰብሰብ የሚያስችለውን መስፈርት ካሟላ የብቃት ማረጋገጫ አግኝቶ ናሙና የመሰብሰብ ሥራን በተጨማሪነት መፈጸም ይችላል፡፡

14.2. በናሙና አውጭነት የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል የመስክ ጥራት ተቆጣጣሪነትን ተግባር ማከናወን አይችልም፡፡

## ክፍል አምስት

## ዘር ወደ አገር ውስጥ አስገብቶ ለማከፋፈል እና ወደ ውጭ ለመላክ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርቶች

15. የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ

15.1. በዕፅዋት ሳይንስ ወይም በሆርቲካልቸር ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ወይም የተጠቀሰውን የሙያ ደረጃ ያለው ባለሙያ የቀጠረ፤

15.2. በዕፅዋት ዘር ማስመጣትና መላክ ቢያንስ አንድ አመት ወይም በዕፅዋት ዘር ዘርፍ አንድ አመት የስራ ልምድ ያለው ወይም ባለሙያ የቀጠረ፡፡

16. ስለ ዘር ማቆያ መጋዘን

16.1. ለመስክና ለጥራጥሬ ሰብሎች በአንቀጽ 10 በተጠቀሰው መስፈርት መሠረት ለዘር ማቆያ የሚሆን መጋዘን በባለቤትነት ያለው ከሆነ ህጋዊ ካርታ ወይም በኪራይ ከሆነ ህጋዊ ውል ማቅረብ አለበት፡፡

16.2. በአንቀጽ 10 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የመጋዘኑ ስፋት ለአትክልት እውን ዘር ሲሆን አገሪቱ ባጸደቀችው የሎት ደረጃ መሰረትና እንደቀረበው ዘር መጠን ማስደርደር የሚያስችል መጋዘን በባለቤትነት ያለው ከሆነ ህጋዊ ካርታ ወይም በኪራይ ከሆነ ህጋዊ የኪራይ ውል ማቅረብ አለበት፡፡

16.3. ለችግኝ፣ ለአኩራች ዘር፣ ለቁርጥራጭ፣ ለስራስር ማከማቻ ስለሚሆን መጋዝን የተቆጣጣሪው አካል ኢንስፔክተር በሚሰጠው የሙያ አስተያየት የሚወሰን ይሆናል፡፡

17. ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገባ የዕፅዋት ዝርያ

በሌላ የሚኒስቴሩ መመሪያ ካልተደነገገ በስተቀር ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዝርያ በሀገሪቱ ውስጥ የማላመድ ሙከራ ተሰርቶ ተስማሚ ሲሆንና በዝርያ መዝገብ ሲመዘገብ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ስድስት

## ዘር ለማከፋፈልና ለመቸርቸር የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መስፈርቶች

18. ዘር ለማከፋፈል

18.1. ዘር በማከፋፈል ስራ የሚሰማራ ግለሰብ ወይም የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ወይም ዘር አምራች ድርጅት ሊሆን ይችላል፤

18.2. አንድ ዘር አከፋፋይ ዘር አምራች ካልሆነ ከተለያዩ ዘር አምራቾችና አስመጪዎች ዘር ተቀብሎና በአግባቡ በሎት መሰረት አከማችቶ መሸጥ ይችላል፤

18.3. ዘር ለማከፋፈል የሚሰማራ አካል በዕፅዋት ሳይንስ/ በሆርቲካልቸር/ በጠቅላላ እርሻ ሙያ ቢያንስ ዲፕሎማ ትምህርት ዝግጅትና በዘር ግብይት ቢያንስ የአንድ አመት የሥራ ልምድ ያለው ወይም የተጠቀሰውን የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ያለው ባለሙያ መቅጠር የሚችል መሆን አለበት፤

18.4. የዘር አምራች ድርጅቱ የራሱን ዘር ብቻ የሚያከፋፍል ከሆነ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት እና ለማከፋፈል የብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ሊኖረው ይገባል፤

18.5. በአንቀጽ 10 በተጠቀሰው መስፈርት መሰረት ለዘሩ ማቆያ የሚሆን መጋዝን በባለቤትነት ወይም በኪራይ ያለው፣ በባለቤትነት ከሆነ ህጋዊ ካርታ፣ በኪራይ ከሆነ በውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የኪራይ ውል ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

19. ዘር መቸርቸር

19.1. ዘር ቸርቻሪ ግለሰብ ወይም የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ሌሎች አካላት ሊሆኑ ይችላል፤

19.2. ቸርቻሪው ለመቸርቸር የሚሆነውን ዘር የብቃት ማረጋገጫ ካገኙ የተለያዩ አምራቾች ወይም ዘር አከፋፋዮች በቀጥታ ግዥ ወይም በወኪል ሻጭነት ሊረከብ ይችላል፡፡

19.3. ዘር አምራች መቸርቸር የሚፈልግ ከሆነ ተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፤

19.4. ዘር ለመቸርቸር የሚሰማራ አካል

ሀ. ግለሰብ ከሆነ ቢያንስ አስረኛ ክፍል ስለማጠናቀቁ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ወይም እርሱ ያላጠናቀቀ ከሆነ ሌላ ሰው በሻጭነት መቅጠር አለበት፤

ለ. ለማህበራት ሲሆን የማህበሩ ተቀጣሪ ለሽያጭ የመጋዘን ወይም የሂሳብ ሰራተኛ ስልጠና የወሰዱትን እንደ ዘር ሻጭ መመደብ አለበት፤

ሐ. የስራው ባለቤት ወይም ተቀጣሪው ቢቻል በዕፅዋት ዘርና ሌሎች ግብአቶች ሽያጭ 6 ወር የስራ ልምድ ያለው ወይም በዕፅዋት ዘር ሽያጭ የሁለት ሳምንት ስልጠና የወሰደና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

19.5. ዘር በመቸርቸር ስራ የሚሰማራ አካል የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው በአንድ ጊዜ በመጋዘኑ ውስጥ የሚያቆየው የዘር መጠን እስከ 300 ኩንታል ሆኖ

ሀ/ የመስክና ጥራጥሬ ሰብሎች ዘር ከ3 ወር ላልበለጠ ጊዜ የማይቆይ ሲሆን፣

ለ/ የአትክልት ዘርን በተመለከተ ግን ከአንድ ዓመት በላይ የማይቆይ ከሆነ ነው፤

ሐ/ የፍራፍሬ/አትክልት ችግኝ፣ኮረት፣ኮርም፣ቁርጥራጭ በተመለከተ ግን እንደ ወቅታዊ ይዞታቸው እየታየ የቆይታ ጊዜአቸው በባለሙያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

19.6. በዘር ዝግጅት እና በአከፋፋይነት የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል በችርቻሮ ስራ ለመሰማራት ተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ ማውጣት ይኖርበታል፤

19.7. የዘር ማከማቻው ራሱ ያፈራው ንብረት የሆነ ወይም በስጦታ ወይም በኪራይ የተገኘ መጋዘን ወይም መኖሪያ ቤት ሆኖ የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ ሊሆን ይገባል፡፡

ሀ. ወለሉ ኮንክሪት የሆነ፣

ለ. ዘሩ የሚቀመጥበት ፓሌት የተሰራለት፣

ሐ. ግድግዳው አይጥ የማያስገባ ሆኖ የተሰራ፣

መ. ከማዳበሪያና ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ክምችት የጸዳ፣

ሠ. መስኮቶቹ አየር የሚያስገባ ከሽቦ የተሰራ ወንፊት የተገጠመለት፣

ረ. መጋዘኑ የዘር አደራደር ሎትን መሰረት አድርጎ ለመደርደር የሚያስችል አቅም ያለው፣

ሰ. የአትክልትና መኖ ዘር ለመቸርቸር የተሰማራ አካል የዘር መደርደሪያ ሽልፍና ቢያንስ ስድስት ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ሱቅ ሊኖረው ይገባል፡፡

## ክፍል ሰባት

## በብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ የፌደራል እና የክልሎች ሀላፊነትና ተግባር

20. የፌደራል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ኃላፊነት እና ተግባር

20.1. ማንኛውም የዘር አምራች፣ አዘጋጅና አከፋፋይ ስራው ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚሸፍን ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ችግር ካለበት ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤

20.2. ዘር ወደ ውጭ ለመላክና ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ለመሰማራት ለሚፈልጉ አካላት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፣ ችግር ካለበት ያግዳል ወይም ይሰርዛል፡፡

21. የዘር ጥራትን ለመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው የክልል ባለስልጣን ሀላፊነትና ተግባር

ማንኛውም የዘር አምራች፣ አዘጋጅ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ስራው በአንድ ክልል ተወስኖ የሚካሄድ ሲሆን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፣ ችግር ካለበት ያግዳል ወይም ይሰርዛል፡፡

## ክፍል ስምንት

## በዘር ስራ ለመሰማራት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው አካልመብትና ግዴታዎች

22. በዘር ስራ የተሰማራ አካል ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ሊጠበቁለት የሚገቡ መብቶች፣

22.1. የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አምራች የመነሻ ዘር ከሚያቀርብ ከማንኛውም ተቋም አስቀድሞ ውል በመግባት ለዘር ማምረት የሚሆን መነሻ ዘር የማግኘት መብት ይኖረዋል፤

22.2. መነሻው ዘር ከልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ በበቂ መጠን ያልተዘጋጀ ከሆነ እጥረቱን ተከትሎ አግባብ ባለው የክልል ወይም የፌደራል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ተቋም በሚዘጋጀው ድልድል መሠረት እንዲካተት ይደረጋል፤

22.3. ያመረተውን ዘር ተቆጣጣሪው አካል ካረጋገጠ በኋላ ቀጥታ በራሱ ድርጅት ወይም የሽያጭ ወኪል በመመደብ ለአርሶ አደሮች በተለያየ የእሽግ መጠን ማከፋፈል ይችላል፤

22.4. የብቃት ማረጋገጫ ከፌደራል ያገኘ አካል የክልሎቹን እውቅና በማግኘት ዘሩን በአገሪቱ ባሉ ክልሎች ሁሉ ማከፋፈል ይችላል፤

22.5. ዘሩ የሚመጣበትን አገር ፋይቶሳኒተሪ ሰርተፊኬት እስከአቀረበ ድረስ ከውጭ ለማስገባት የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ዘር አስመጪ አካል ያመጣው የአገሪቱን የዘር ፋይቶሳኒተሪ መስፈርት አሟልቶ የዘር ጥራት ቁጥጥር ሠርተፊኬት ሲያገኝ ዘሩን በአገር ውስጥ የማከፋፈል መብት ይኖረዋል፤

22.6. የኢትዮጵያን ፋይቶሳኒተሪ ሰርተፊኬት እስከአገኘ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ዘር ላኪ የዘር ጥራት ቁጥጥር ሰርተፊኬት ያገኘን ዘር ከአገር ውጪ የመላክ መብት ይኖረዋል፤

22.7. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል ከህገወጥ የዘር ንግድ የመጠበቅ መብት አለው፤

22.8. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል የመስክ እና የላቦራቶሪ ዘር ጥራት ቁጥጥር ስራ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለስልጣን ተፈጻሚ ሲሆን በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ መስፈርት መሰረት ካልተከናወነ አግባብ ላለው የፌደራል ወይም የክልል የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፤

22.9. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል የዘር ጥራት ማረጋገጫ ውጤት ሪፖርት ከተቆጣጣሪው አካል የማግኘት መብት አለው፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture & Natural Resources

22.10. በአንድ ክልል ተወስኖ ዘር ለማምረት የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል ያመረተው የሰብል ዝርያ ዘር በሌላ ክልል ተፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ዘሩ የተመረተበት ክልል እና ዘሩ የተፈለገበት ክልል የተስማሙበትን ደብደቤ ለፌደራል በማቅረብ አግባብ ካለው የፌደራል ተቆጣጣሪ አካል በሚሰጠው የድጋፍ ደብዳቤ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

23. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያገኘ አካል ግዴታዎች

23.1. ማንኛውም አካል የዘር ንግድ ፈቃድ ለማግኘት አስቀድሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት ይጠበቅበታል፤

23.2. ዘር ለማምረት የሚውለው ዝርያ የዕፅዋት ዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ መሆን ይኖርበታል፤

23.3. በሌላ የሚኒስቴሩ መመሪያ ካልተደነገገ በስተቀር ያልተመዘገበ ዝርያ ዘር ፣ ምንጩ የማይታወቅ ዘር እና የዘር ጥራት ቁጥጥር ያልተደረገበት ዘር ለሽያጭ ገበያ ይዞ መቅረብ አይቻልም፤

23.4. የዘር ማምረቱ ሥራ የሚከናወነው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ባወጣው የዘር መስፈርት መሰረት መሆን ይገባዋል፤

23.5. የዘር ማምረቱ ስራ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የመስክ ዘር ጥራት መስፈርቶች መሠረት መከናወኑን ለሚያረጋግጠው የክልል ወይም የፌዴራል ባለስልጣን ለዘር ተቆጣጣሪ ኢንስፔክተር የመስክ ጥራት ቁጥጥር ስራ የመተባበር ግዴታ አለበት፤

23.6. የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያገኘ አምራች በመስክ ደረጃ የዘር ጥራት ቁጥጥር ከተደረገ በኋላ ሊወገዱ/ሊስተካከሉ በተቆጣጣሪው አካል አስተያየት የተሰጠባቸውን ጉዳዮች ተከታትሎ መፈጸም ይኖርበታል፤

23.7. የጥራት ቁጥጥሩን ያለፉ ማሳዎች ላይ ዘር ለመሰብሰብ ትክክለኛውን የእርጥበት መጠን መድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

23.8. በዘር ዝግጅት ሂደት ዘር ጥራቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ አግባብነት ካለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ባለሙያ ጋር ተባብሮ የመስራት ግዴታ አለበት፤

23.9. የዘር ሎት አደራደሩ በሁሉም አቅጣጫ እና ከፍታው ለናሙና አወሳሰድ አዳጋች እንዳይሆን ተደርጎ መደርደር ይኖርበታል፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture & Natural Resources

23.10. የዘር ዝግጅቱ ስራ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የዘር ጥራት መስፈርት መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ የዘር ናሙና የመስጠት ግዴታ አለበት፤

23.11. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል አግባብነት ካለው ተቆጣጣሪ አካል የሚሰጠውን የዘር መለያ ምልክት የዘር ጥራት ማረጋገጫ በተሰጠው ዘር ላይ ብቻ የማያያዝ ግዴታ አለበት፤

23.12. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል በዘር ከረጢት ላይ የሚያይዘው የዘር መለያ ምልክት የዘሩን ምንነት በትክክል የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፤

23.13. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም የተሳሳተን የዘር መለያ ምልክት መጠቀም የለበትም፤

23.14. የዘር ጥራት ቁጥጥር ተደርጎ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ የዘር ጥራት መስፈርትን የማያሟላ መሆኑን አግባብነት ካለው የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ሲገለጽ ከወደቀ የዘር ማሳ የተገኘው ምርትና የወደቀ የዘር ሎት ለዘር እንዳይውል ማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

23.15. ጥራቱ በተገለጸ ዘር ስርአት እና በመደበኛ ዘር ስርአት የተመረተን ዘር አንድ መጋዘን ውስጥ አስቀምጦ መሸጥ አይችልም፤

23.16. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኘ አካል የሚያከፋፍለው ወይም የሚቸረችረው ዘር የብቃት ማረጋገጫ በተሰጠው አካል የተመረተ መሆኑንና አግባብነት ያለው የክልል ወይም የፌደራል ተቆጣጣሪ አካል የዘር ጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተለጠፈበት መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

23.17. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ዘር አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ የታሸገን የዘር ከረጢት ወይም ሌላ የዘር መያዣን ከፍቶ መሸጥ አይችልም፤

23.18. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል ከአንድ ምርት ዘመን ያደረ ዘር ለቀጣይ ምርት ዘመን ለመጠቀም ከተፈለገ ከዘር ወቅት አስቀድሞ ሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ አካል ስለ ጥራት ሁኔታው ማስፈተሽና የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት ይኖርበታል፤

23.19. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል ለፍተሻ ያቀረበው የዘመኑ አዲስ የገባ ዘርም ሆነ ካለፈ ምርት ዘመን ያደረ ዘር በዘር ንጽህና ፍተሻ ሲወድቅ የወደቀውን

ዘር ከረጢት በመፍታት እንደገና እንዲበጠር ማድረግና የድጋሚ ፍተሻ ጥያቄ አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ አካል የዘር ወቅት ከማለፉ በፊት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

23.20. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ ዘር አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ በዘር ግብይት ሂደት አግባብነት ያለው ተቆጣጣሪ አካል የዘር ጥራት ጉድለት እንደተከሰተ ጥርጣሬ ሲያድርበት የዘር ጥራት ማረጋገጫ ከተሰጠው ዘር ላይ ናሙና ወስዶ ድህረ-ቁጥጥር ፍተሻ ሲያደርግ ትብብር ማድረግ ይኖርበታል፤

23.21. ከአንድ ክልል በላይ እንዲሠራ የፌደራል ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኘ አካል ዘሩን ካመረተበት ክልል ውጭ ለማከፋፈል ሲፈልግ ያመረተበት ክልል እና ተቀባዩ ክልል ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች እውቅና ሊሰጡት ይገባል፤

23.22. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል አግባብ ባለው የተቆጣጣሪው አካል ኢንስፔክተር ሲጠየቅ ከዘር ጥራት ቁጥጥር ጋር በተያያዙ ጉዳዮች መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

23.23. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ያገኘ አካል የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማሳደስ ሲመጣ በየደረጃው የተጠቀሰው መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፣

24. ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የዕጽዋት ዘር ብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ ተመን የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 361/2008 ዓ.ም የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

25. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለአንድ አመት ይሆናል፡፡

26. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድ፣

26.1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

ሀ. የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን ሁኔታዎች ጠብቆ ማቆየት ካልቻለ፤

ለ. በዚህ መመሪያ ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች እና ስለዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡትን ደንቦች ወይም ሌሎች

መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል ባለስልጣን ጉድለቶቹን ከ15 እስከ 35 ባሉት ቀናት ውስጥ እንዲያስተካክል በማስገንዘብ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል፡፡

27. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

27.1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

ሀ. የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ፣

ለ. ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ ወይም

ሐ. ስለዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 26 ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡትን ደንቦች ወይም ሌሎች መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት ፈጽሞ ከተገኘ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

27.2. በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ተላልፎ ሲገኝ ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን የሰረዘ እንደሆነ ወረቀቱ ላይ ተመስርቶ የተሰጠው የንግድ ፈቃድ እንዲሰረዝ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጭ አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል አስር

## ስለ ቅሬታ አቀራረብ

28. ስለዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 25 እና ይህን መመሪያ መሰረት ተደርጎ በተሰጠ ማንኛውም ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔውን ካወቀበት ጀምሮ ቅሬታውን ውሳኔ ለሰጠው የፌዴራል ወይም የክልል የተቆጣጣሪው አካል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ማዕከል በአምስት ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

29. አግባብ ያለው የፌዴራል ወይም የክልል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ማዕከል ቅሬታው በደረሰው በአስር ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

30. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 30 በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን አግባብ ላለው የፌዴራል ወይም የክልል ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በአምስት ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

31. አግባብ ያለው የፌዴራል ወይም የክልል ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ቅሬታው በደረሰው በአስር ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

32. ቅሬታ አቅራቢው በባለስልጣኑ የተሰጠው ውሳኔ ካላረካው ቅሬታውን ለሚመለከተው የፍትህ አካል በ30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

33. መመሪያው የሚፈፀምበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ የካቲት 1 ቀን 2010 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

እያሱ አብርሃ (ዶክተር)
እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር
አዲስ አበባ